## ትምህርት 2

**የሰው ዘር ሁሉ በኃጢአት ምክንያት መውደቁ፡-**

እግዚአብሔር አዳምና ሄዋንን ሲፈጥር በራሱ አምሳል ኃጢአት የሌለባቸው አድርጎ ፈጠራቸው፡ ፡ አዳምንም መልካምና ክፉውን ከምታሳውቅ ዛፍ አትብላ ምክንያቱም ከእርሷ በበላህ ቀን በእርግጥ ትሞታለህ የሚል ግልጽና ስፔሲፊክ (ልዩ) የሆነ ትዕዛዝ (ሕግ) ሰጠው። የተሰጠውን ትዕዛዝ መጠበቅ አለመጠበቅ የአዳም ኃላፊነትና ምርጫ ነበረ። የወደፊት ሕይወቱ መልካም ወይም የከፋ የሚሆነው የተሰጠውን ትዕዛዝ እግዚአብሔርን አምኖ በመታዘዙ ወይም ባለመታዘዙ ነበረ። አዳም ግን የተሰጠውን ትዕዛዝ በመጠበቅ አልጸናም። አዳም እግዚአብሔር የተናገረው ቃል እውነት እንደሆነ አምኖ መቀጠል ሲገባው ሰይጣን የተናገረውን ውሸት አምኖ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ በመጣሱ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው የቅርብ ወዳጅነት ባርኮት አጥቶ የሰይጣን፣ የሞትና የመርገም ተገዢ ሆነ።

እግዚአብሔር ምድርና በውስጧና በውጫዊ ገጽዋ ያሉት ፍጥረታት ሁሉ የሰው ዘር እንዲጠቀምባቸውና እንዲገዛቸው ስልጣን ሰጥቶ የነበረ ሲሆን አዳምና ሔዋን አግዚአብሔርን አምነው ሊገዙለት ሲገባ ሰይጣንን አምነው የነገራቸውን ውሸት ተቀብለው ስለታዘዙት (እንደ መራቸው በፈቃደኝነት ስለተመሩለት) ምድርን የመግዛት ስልጣናቸው ለሰይጣን ስላስረከቡ ሰይጣን የዚህ ዓለም ገዢነት አገኘ (ገዢ ሆነ)።

ስለዚህ ማንኛውም ሰው እግዚአብሔርንና ቃሉን አምኖ የሚታዘዝ ካልሆነ የሚያደርገው ነገር በራሱ ፈቃድ በመመራት ወይም ሰይጣን እንደመራው የሚጓዝ ስለሚሆን፣ በእግዚአብሔር ላይ በማመጽ ቢገባውም ባይገባውም የሰይጣን ወዳጅ በመሆን በራሱ ላይ ሰይጣንን ገዢ አድርጎ ይሾሟል ማለት ነው፡

**የኃጢአት ትርጉም፡ -**

1ኛ ዮሐ 3፡4፣ "ኃጢአት የሚያደርግ ሁሉ ዓመጽን ያደርጋል፤ ኃጢአትም ዓመጽ ነው" ይላል፡፡ ስለዚህ ኃጢአት ማለት በእግዚአብሔር ትዕዛዝ/ሕግ/ፈቃድ ላይ ማመጽ ማለት ነው፡፡

በተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ውስጥ ኃጢአት ለሚለው ቃል እንደ አውዱ የሚከተሉት ተዛማጅ ትርጉሞች አሉት፡፡ እነዚህም የእግዚአብሔርን ህግን መጣስ፣ ያልተፈቀደ መስመር/ድንበር መተላለፍ፣ እግዚአብሔርን አለመታዘዝ/ለቁጣ ማነሳሳት፣ አግዚአብሔር ለሰው ያዘጋጀውን የጽድቅ ስታንዳርድ ግብ መሳት፣ ከአግዚአብሄር በመኮብለል/በመሰደድ ወይም በመለየት በግል ፈቃድ/መንገድ መሄድና በደል መፈጸም የሚሉ ናቸው፡፡

**ስለዚህ ማንኛውም ሰውን የሚበድል እግዚአብሔርን የሚያሳዝንና ክብሩን የሚጋፋ ክፉ ተግባር፣ ክፉ ንግግርና ክፉ ሃሳብ ሁሉ ኃጢአት ነው፡፡** (ዘዳ 9፡7፣ ኢሳ 53፡5፤ 59፡2፤) እግዚአብሔር ፍጹም ቅዱስ ስለሆነ ኃጢአትን ይጠላል፡፡

በኃጢአት መካከል የደረጃ ልዩነት እንዳለ ይታያል፤ ማለትም እግዚአብሔር ማንኛውንም ኃጢአት የሚጠላ ቢሆንም አንዳንድ ሃጢአትን ከሌላኛው ይልቅ ያከብደዋል፡፡ የሚከተለትን ሁለት አስረጂዎች ይመልከቱ፡፡

ማቴዎስ 23፥23 “እናንት ግብዞች የኦሪት ሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን፤ ወዮላችሁ! ከአዝሙድ፣ ከእንስላልና ከከሙን ዐሥራት እየሰጣችሁ በሕጉ ውስጥ ዋነኛ የሆኑትን ማለትም ፍትሕን፣ ምሕረትንና ታማኝነትን ግን ንቃችኋልና፤ እነዚያን ሳትተዉ እነዚህን ማድረግ በተገባችሁ ነበር፤”

ምሳሌ 6፡16-19፣ "እግዚአብሔር የሚጠላቸው ስድስት ነገሮች አሉ፤ የሚጸየፋቸውም ሰባት ናቸው፤ እነርሱም፦[17] ትዕቢተኛ ዐይን፣ ሐሰተኛ ምላስ፣ ንጹሕ ደም የሚያፈሱ እጆች፣ [18] ክፋትን የሚያውጠነጥን ልብ፣ ወደ ክፋት የሚቻኰሉ እግሮች፣ [19] በውሸት ላይ ውሸት የሚጨምር ሐሰተኛ ምስክር፣ በወንድማማቾች መካከል ጠብን የሚጭር ሰው"።

ነገር ግን ከመዋሸት ጀምሮ በማንኛውም ኃጢአት ጸንቶ መቀጠል የዘላለም ሞት ፍርድ ያስከትላል፡፡

**የኃጢአት ዓይነቶች፡-** የኃጢአት ዝርዝር ብዙ ቢሆንም ለጥናት እንዲያመች ሁሉም ኃጢአት በተወሰኑ ክፍሎች ወይም መደቦች መከፋፈል ይቻላል፡፡ እነዚህም፡-

- ይቅር የማይባል፡- ምሳሌ፤ በእግዚአብሔርና በቃሉ ዕውነት አለማመን፣ መንፈስ ቅዱስን መሳደብና ጌታ ኢየሱስን አምነው በመቀበል የተወሰነ ጊዜ ከቆዩ በኋላ መልሶ መካድ እግዚአብሔር ይቅር እንደማይላቸው በቃሉ የገላጻቸው ናቸው፣ ማር 3፡28-29፤ ዮሐ 3፡16-18፣ ዕብ 6፡6፡፡
- ይቅር የሚባል፡- ከላይ ከተጠቀሱት ሶስቱ ኃጢአት በስተቀር ከልብ በመጸጸትና በንስሀ ተመልሰው ምህረት በመጠየቅ የንስሃ ፍሬ ካፈሩ ማንኛውም ኃጢአት ይቅር ይባላል፡፡ የሰውን ኃጢአት ይቅር በማለት ማጽደቅ የሚችለው ራሱ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ሕዝቅኤል 18፡23፣ 33፡11-16፣
- ባለማወቅ የሚፈጸም፡- በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ኃጢአት ነው ተብሎ የተጠቀሰ ነገር በቃሉ መኖሩን ሳያውቁ መፈጸም ኃጢአት መሆኑን በተረዱ ጊዜ ንስሃ መግባት ይጠይቃል፡፡
  (ኃጢአት መሆኑን ሳያውቁት ጽድቅ እየመሰለ የሚፈጸም፤ ምሳሌ፣ አይሁድ ጌታ ኢየሱስን ያስገደሉት ይመጣል ብለው ሲጠባበቁት የነበረው መሲህ መሆኑን ባለማወቃቸውና አሳች ነው ብለው በመገመታቸው ነው፡፡)
- የድፍረት/ሆን ተብሎ የሚፈጸም፡- ኃጢአት መሆኑና እግዚአብሔር እንደሚያዝንበት እየታወቀ ሆን ተብሎ የሚፈጸም ድርጊት ወይም ንግግር ነው፡፡
- በድንገት የሚፈጸም/accidental፡- ለምሳሌ ሳያውቁ በድንገት ሊጎዱት ያልፈለጉትን ሰው ንብረት፣ ስሜት፣ አካል መጉዳት፡፡

- የግለሰብ፡- እንድ ሰው ብቻውን የሚፈጽመው፣ የቤተሰብ፡- በቤተሰብ አባለት የሚፈጸም፣ የማሕበረሰብ፡- በአንድ በአንድ አካባቢ ነዋሪዎች የሚፈጸም፤ … የሀገር፣ የዓለም ኃጢአት ተብሎ ሊዘረዘር ይችላል፡፡

የትምህርት 1 ጥያቄዎች

1. አዳምና ሄዋን ሲፈጠሩ አትብሉ የተባሉት ዛፍ ፍሬ እስከ በሉበት ዕለት ድረስ ኃጢአተኞች ነበሩ ወይስ ጻድቃን?
2. የኃጢአት ትርጉም ምንድነው?
3. እግዚአብሔር ይቅር የማይለው ኃጢአት ምሳሌ ጥቀስ፤
4. ይቅር የሚባል ኃጢአት ምሳሌ ጥቀስ፤
5. አንተ የሰራኸው ኃጢአት እንዳለ ታስታውሳለህ?
6. የሰውን ኃጢአት ሁሉ ይቅር ማለት የሚችለው ማነው?
7. ሰው ለሰራው ኃጢአት ምህረት/ይቅርታ ለማግኘት ምን ማድረግ አለበት?